# ኢትዮጵያውያኑ አላዊቶች

ይነጋል በላቸው

አንዳንድ ‹ኢትዮጵያውያን› ድረ ገጾች እኔ የምልክላቸው ብሶት ወለድ ሀተታ ሳይጥማቸው እዬቀረ የ‹ትራሽ› ሣጥናቸው ቀለብ አድርገው ቢያስቀሩትም ሃሳቤን መግለጼን አልተውም፡፡ ደግሞም ወላድ በድባብ ትሂድ የኢትዮጵያ አምላክም በሥራቸው ሁሉ ይባርካቸው ከራሳቸው ጠባብ ፍላጎት ይልቅ ለሃሳብ መንሸራሸር ቅድሚያ የሚሰጡ ስላሉ የማያሳፍሩኝ ድረ ገጾች አሉ፤ ልጅ ይውጣላቸው፡፡ ‹ሂዳችሁ ቃሌን አድርሱ፤ እምቢ ቢሏችሁ የእግራችሁን አቧራ አራግፋችሁ ከዚያ ቦታ ውጡ…› ይላቸው ነበር ጌታቸን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ፡፡ እኔ ኃጢያተኛው ወዲ በላቸውም እንዲህ እላለሁ - «በመሠረቱ ማንም የማንንም ብሶትና የሰቆቃ ዋይታ የማዳመጥ ግዴታና ታሪካዊ የኃላፊነት ሸክም የለበትም፤ ነገር ግን ‹ሲሞቅ በማንኪያ ሲቀዘቅዝ በእጅ› እንደሚባለው እንዳይሆን ነገሮችን ከራስ ጥቅምና ፍላጎት ብቻ በማቆራኘት ሂደት ሊፈጠር ከሚችል ጠባብ የአለመግባቢያ ዐውድ በአፋጣኝ  ለመውጣት እንሞክር፡፡ የሚወዱትን ቅላጼ ብቻ እየመረጡ ማዳመጥ አዲስ ሳይሆን ጥንትም ነበር፡፡ ዘመኑ የመደማመጥና የመቻቻል መሆን ይኖርበታል፡፡ አዲስ የወይን መጠጥ በአሮጌ ጠርሙስ መክተት ይብቃ፡፡ በወያኔና መሰሎቹ እጅ እጅ ያለን አፈናና እመቃ በተስፈኛ የወደፊት ዴሞክራት ኃይላት  መንደር ውስጥ መታዘብ ያሳፍራል፤ ያስፈራልም፤‹በጊዜ የጮኸ ጅብ አያሳድረኝም› እንደምንል፡፡ በፀጉር ስንጠቃ የአንድ ቃል ወይም ሐረግ ስንጥርጥር የአንድምታ ትርጓሜ ስንቸገር ጊዜው በከንቱ እየሸመጠጠብን ሊመሽብን ነው፡፡ በዚያ ዓይነቱ ያፈጀ ያረጀ ተግባር አንጠመድ፡፡ ላስተዋለ ግዑዛን ነገሮችም ሳይቀሩ ይናገራሉና የመደማመጥና የመግባባት ክሂላችንን አድማስ እናስፋ፤በዚህ እንጠቀማለን እንጂ አንጎዳም፡፡… » የአባት ምክር ጠቃሚ ነውና - ንሃቦ ዕዝን ወልቦና - ግዕዝ ነገርን ያጣፍጣል፡፡

ማርዋን ቢሻራ የሚባለው የአልጀዚራ ሲኔየር የፖለቲካ ትንተና ጋዜጠኛ በሦርያ የፖለቲካ ቀውስ ዙሪያ ሦስት እንግዶችን ጋብዞ እያነጋገረ ነው  አሁን - አቋርጬው ከመምጣቴ በፊት፡፡ እየተነጋሩበት ያለው ነገር ከኢትዮጵያ ጉዳይ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ በመሆኑ ከአሁን አሁን ጨርሰው እኔም ወደወረቀቴ እሄዳለሁ ስል ንግግራቸውን እንዳልጨርስ ያደረገኝን የአንደኛውን ሰው አስተያየት እንዲህ ሲነገር ሰማሁና አልቻልኩም፤ ትቼው መጣሁ፡፡

ጠያቂ፤ እሳቸው እንደተናገሩት (ሌላ አስተያየተኛ የተናገረውን በመጥቀስ) የሦርያ ጦር ውስጥ በርካታ ሱኒዎች ካሉና በየጊዜው ጦሩን እየከዳ ወደተቃዋሚው ጎራ የሚቀላቀለው የሠራዊት አባል ብዙ ከሆነ ለምንድን ነው የንዑሳኑ ገዢ መደብ የአሳድ መንግሥት በቀላሉና በአፋጣኝ ሊወድቅ ያልቻለውና የማይችለው?

መላሽ፤ እንደሱ እማይሆንበት ብዙ ምክንያት አለ፡፡ በዋናነት የሚጠቀሰው ምንም እንኳን በጦሩ ውስጥ የተጨቋኙ የብዙኃኑ ሱኒዎች አባላት በብዛት ቢኖሩም ከፍተኛ መኮንኖችና የጦር አዛዦች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ሥልጣኑን የያዙት የገዢው የአላዊት ጎሣ አባላት ናቸው፡፡ ከ1200 የጦር አመራር ከፍተኛ አዛዦች መካከል ከ1000 በላይ የሚሆኑት አላዊቶች ናቸው፡፡ (እነሱም በዓይነ ቁራኛ የሚታዩ፣ በሥለላ መረብ እያንዳንዷ እንቅስቃሴያቸው እየተመዘገበች የምትያዝና ለስሙ ያህል ሱኒዎችን ለማታለል የተቀመጡ ናቸው፤ የቅንፏ ጭማሪ - እውነትነቷ እንደተጠበቀ ሆኖ - የኔ ናት) ስለዚህ አመራሩና ሁሉም የሀገሪቱ እንቅስቃሴ በአላዊቶች ሥር በመሆኑ የአሳድን መንግሥት ጦር ለማፍረክረክና ሥልጣኑን ከጠባብ ጎሠኞች ወደብዙኃኑ ለማዛወር ጊዜ መውሰዱ አይቀርም፡፡

የነገሮች መመሳሰል እጅግ ደነቀኝና እየተናገረ ያለው ሰው ተናግሮ በቅጡ ሳይጨርስ እኔም ሳልረሳው በቀጥታ ወደጽሑፌ መጣሁ፡፡

ኢትዮጵያውያን ታዲያ ከዚህ ምን ልንገነዘብ እንችላለን?

ቀደም ባለ ወቅት ግንቦት ሰባት ባወጣው አንድ ጥናታዊ መረጃ ከዚያን ጊዜው የኢትዮጵያ 62 ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ውስጥ አራቱ ብቻ ከትግሬ ውጪ ሲሆኑ ሌሎቹ በሙሉ የወያኔ ትግሬዎች መሆናቸውን ማንበቤ ትዝ ይለኛል፤ አልገረመኝም አይገርመኝምም፡፡ አሥራ ሰባት ዓመት አፈር ልሰው ድንጋይና እባብ ተንተርሰው፣ በሱዳንና በሕንድ አንደርባዊ የአፍዝ አደንግዝ  ድግምት ነፍስ ዘርተው የታገሉለትን ድል በስመ ዴሞክራሲ እንዴት አሳልፈው ይሰጣሉ? ጅሎች እኛ እንጂ እነሱ ብልጥ የብልጥ ብልጥ ናቸው፡፡ እንዲያውም አሁን አንድም የሌላ ጎሣ

Ethiopia Will Prevail!

ወይም ብሔረሰብ አባል የጦር መኮንን ያለ አይመስለኝም፡፡ ቢኖርም እንደሌላው ሁሉ ከፍ ሲል በቅንፍ እንዳስቀመጥኩት ለይስሙላና ክፍተት ለመሙላት ካልሆነ በስተቀር በእውናዊ ሥልጣን በተለይ የአማራና የኦሮሞ ብሔር አንድም አባል በወታደራዊ የዕዝ ሰንሰለት ውስጥ ሊኖር እንደማይችል አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል፡፡ እንዴት ብሎ? በሌላው ሥልጣን ሳይቀር ከጽዳትና ዘበኛ እስከ ከፍተኛ ሥራ አስኪያጅና ሚኒስትር ድረስ በትግሬ አይደለም እንዴ የተያዘው? ይህን የአደባባይ ምሥጢር መናገር ነው እንግዲህ አንዱ የመደመጫ መድረክ እያሳጣን የሚገኘው፡፡ እንዳይናገር መከልከልስ ይህን የአፓርታይድ ድርጊት የሚፈጽመውን የወያኔንና መሰሎቹን ቡድን ነበር፡፡ እኛማ ቢያንስ ተናግረን እንኳን ይውጣልን እንጂ፡፡

ትንሽ ልቀጥል ይሆን? ኢትዮጵያ ውስጥ እየታዬ ያለው ነገር ከአፓርታይድ በመጠኑ እሚለየው መልካችን አንድ ነው፤ አለባበሳችን ከሞላ ጎደል አንድ ነው፤ ሃይማኖታችን ተመሳሳይ ነው፤ ሥነ ልቦናዊ ቀመራችን አንድ ነበር፤የቋንቋዎቻችን ሥርዎ ግንድ ተመሳሳይ ነው… እርግጥ ነው ወያኔን እግዜር ይስጠው እንደደቡብ አፍሪካውና እንደቀድሞዋ አሜሪካ አፓርታይድ በአንድ ሆቴል እንዳንጠቀምና በአንድ ትራንስፖርት እንዳንሄድ እስካሁን አልተከለከልንም - በዚህ ረገድ እሚታዩ መጠነኛ ችግሮች ቢኖሩም - ሊያውም ልቅበጥ ብሎ ለሚነሣ፡፡ የነጭ ድሃና ሀብታም እንደነበረው ሁሉ የትግሬም ድሃና ሀብታም መኖሩም እውነት ነው፡፡ እንደኛው በችጋርና በችግር እሚቆሉ ትግሬዎች ሞልተዋል ፤ በሥነ ልቦና ግን ጠግበው እንደሚያድሩ የሚያሳምኑን ሁኔታዎች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ሥነ ልቦና ደግሞ የስሜት ሕዋሳትን ለጊዜው በማይጨበጥ ቅዠታዊ ደስታ በደመነፍስ ያስፈነጥዛል እንጂ ጠብ የሚል ቁሣዊ ነገር የለውም፡፡ እነዚህን መሰል ትግሬዎች ወያኔ ወርዶ ከሚከብሩ ይልቅ በድህነት በዚሁ ሥርዓት ቢኖሩ የሚመርጡ ይመስለኛል - አብረን ስለምንኖር እንተዋወቃለን፡፡ ሰው ማለት እንዴቱን ያህል የተረገመ ፍጡር ነው ወንድሞቼ? ከውሻና ከድመትም አንሰን እንገኝ? እነሱ እኮ አብረው ለመደሰትም ይሁን ለመከፋት ውሻነታቸውና ድመትነታቸው ብቻ ነው እሚበቃቸው እንጂ እንደኛ የግንባር ምልክትና የቅንድብ ትልትል እያዩ አይደለም እሚሳሳቡት፡፡ … በተረፈ ማታ ማታ በየዝጉብኙ ዶላር ሳይቀር እንደጉድ ሲረጭ እሚያድር በአብዛኛው ትግሬ ነው፡፡ በዚያ ቦታ አንተ ልትገኝ አትችልም - ግልምጫውንና የፈጣሪነትን ያህል ንዑድነት እሚሰማቸው ወያኔዎች በዘርህና በማንነትህ ላይ የሚነጣጠር ስድብና ዘለፋ እችላለሁ ብለህ ካልቆረጥህ በስተቀር ወደዚያ ቦታ ትውር አትልም፤ ደደብ ከሆንክና ነገር እማይገባህ ከሆንክ መብትህ ነው፡፡ ባጋጣሚ ሄደህ በነሱ ቦታ ብትገኝ እንኳ እንድትወጣ ምቹ ሁኔታ ይፈጠርልሃል፡፡ ‹ውጣ አትበለው እንዲወጣ አድርገው› ይባል የለም? በማን ሜዳ ማን ሊዝናና! ቀድሞ ነገርስ በምንህ ትዝናናለህ? …

ለመሆኑ የተሠራውና እሚሠራው ሕንጻ ሁሉ የማን ነው? ንግዱን ሁሉ በበላይነት ተቆጣጥሮ የሕዝቡን ዕለታዊ እስትንፋስ ሳይቀር በሪሞት ኮንትሮል እሚቆጣጠረው ማን ነው? የገንዘብ እንቅስቃሴው በማን እጅ ነው? ገንዘቡ እንዲህ ጥንቡን እንዲጥል የተደረገው ለምንና በማንስ ነው? መሬቱ ሁሉ የማን ነው? የግልም ሆኑ የመንግሥት የፋብሪካና ኢንዱስትሪ ምርቶችን እሚያዝባቸው ማን ነው? ዝም ብለህ የሀገርህን ጉድ ስማ ወንድሜ - የወያኔ ልጆች እሚማሩት የት ነው? ስንት በሚከፈልባቸው ትምህርት ቤቶች? ከየት በሚገኝ ገቢ? የሌላው ኢትዮጵያዊ ልጆች ደንቁረው እንዲቀሩ ሲደረግ የነቀለሚኖ ት/ቤቶች ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ እንዲማሩ እሚደረገው የማንን የቀብር ሥነ ሥርዓት ለማጣደፍ ነው? የመንግሥትን የእርሻና የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ሥፍራዎች እንደፈለገው እየቸበቸበ የሚከብርና ድሃውን እያፈናቀለ ሀገር እሚያጠፋ ማን ነው? ስሚንቶውን፣ የአርማታ ብረቱን፣ ቆርቆሮውን፣ በጥቅሉ የግንባታና የምግብ ሸቀጦችን የሚያመርትና የሚያስመርት ከሌሎች አምራቾችም እሚረከብ በፈለገው ዋጋም የሚሸጥ ማን ነው? የእርሻ ምርቶችን ከገበሬ በቀጥታ እየገዛ እህል እሚያከማችና ወደውጭ ለዶላር ግብይት እሚልክ በውጤቱም ሕዝብን እሚያስርብና የእህልን ዋጋ እሚያስወድድ ማን ነው? ከብቶችን በጥቁር ገበያ ወደውጭ እየላከ በቀንድ ከብት ከዓለም ሦስተኛ በሆነች ሀገር ሥጋ ለአብዛኛው ሕዝብ ብርቅ እንዲሆን እያደረገ ያለ ማን ነው?(በፊታችን ባለው የ2004 ዓ.ም ፋሲካማ ሥጋ መብላት ሳይሆን ማየትም እምንችል አይመስለኝም፤ እንዲያ እንዳልተጫወትንበት አሁን ሜርኩሪ ሆነ እኮ! ግፍ ሠርተንበት ይሆናል፡ :) አንዱ ዜጋ በሌላው ላይ ጌታና አዛዥ ናዛዥ እንዲሆን በማድረግ ሌላው ዜጋ እንደባሪያ ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲኖር እያደረገ ያለው ማን ነው? የተናርኩት መናገር ከምችለው ግማሽ ያህል እንኳን አይሆንም፡፡ ለመሆኑ ኢትዮጵያ ውስጥ የወረደው ናዳ በቃላትስ ሊገለጽ ይችላል እንዴ? እርግጥ ነው ለተቀማጭ ሰማይ ቅርብ ነው፤ እኛን እያሳበደን ያለው ይህ ዓይነቱ ዐይን ያወጣ መድሎ ለሌላውና ምናልባትም በውጭ ለሚኖረው ምንም ላይመስል ይችላል፡፡ ግን ግን ችግራችን ከዚህም በላይ ነው፡፡ ዜጎችን በየሰበብ አስባቡ እሚያስር እሚገርፍ እሚያሰቃይ እሚገድል እሚያሳድድ እሚያሰድድ ጸጥ እረጭ አድርጎ እሚገዛ በናቡከደነፆራዊ የብረት አርጩሜ ሕዝብን እሚገርፍ በእሳት አለንጋ እሚለበልብ ማን ነው? ከነፍሳችንና ከበደነው ሥጋችን በስተቀር ሁሉንም የሀገሪቱን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ሙሉ በሙሉ በሚቻል ሁኔታ የተቆጣጠረ ማን ነው? ሌላውን እያገባደደ የመነኩሳትን በኣቶችና ገዳማት ሳይቀር በልማት ሰበብ እየተቀራመተ ያለው ማን ነው? አማራ ነው ኦሮሞ? ደራሳ ነው ዳዋሮ?

EthioLion.com

ከምባታ ነው ኮንሶ? ጉራጌ ነው ጠምባሮ? ኣሪ ነው ሙርሲ? ጀምጀም ነው ኩሎ ኮንታ? አደሬ ነው ቆቱ? ሶማሌ ነው አፋር? ሀረሪ ነው ኢሣ?... እናውቃለን ብንናገር እናልቃለን አለች አሉ ማን ናት... የአማራ ነጋዴ አለመኖሩ(አኦ ለጎሊናው ተገዢ የሆነ ሀቀኛ ነጋዴ ማለቴ ነው - ሀቀኛ እሚባል ነጋዴ ካለ) ወይም የኦሮሞ ፖለቲከኛ አለመኖሩ ቆጭቶኝ አይደለም እንዲህ የምብከነከነው፡፡ በጭራሽ! ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ፡፡ የእኔ ፍላጎት ይቺን እዚህ ግባ እማትባልና በአማካይ መጽሐፍ ቅዱሣዊ ሥሌት ሦስት አራተኛዋን ያህል የጨረስኳትን ምድራዊ ዕድሜ በቅጡ እንድኖር ያልተፈቀደልኝ መሆኔን መግለጽ ነው - ሊያውም በገዛ ወንድሞቼና እህቶቼ፡፡ ይህን የአደባባይ እውነት መናገር ምን ያሳፍራል ታዲያ? ምንም! እነሱስ እያፈሩበትም ቢሆን ያውቁት የለም እንዴ? ይሄ ቀን የተገለበጠ እንደሆን በሚል በሃሳብ እሚሸማቀቁ የሉም እንዴ? አብረን ነው እኮ እምንውል ፤ አብረን ነው እኮ እምንኖር - እየተገለማመጥን፤ እየተፋቀርንም እየተጎሻመጥንም፡፡ ለምን ቢባል የችግሩ መገለጫዎች እነሱና እኛ መሆናችን ባይካድም የችግሩ ፈጣሪዎች በአብዛኛው እኛም ሆንን እነሱ ባለመሆናችን፡፡ ችግራችን ቀንዱና ብዙው የሰውነቱ ክፍል እዚሁ ይመስለኛል ጭራው ሌላ ቦታ ነው ግን - ምናልባትም ‹እታችኛው ሰማይ›[the netherworld]፡፡ በየዕድሩ በየመሥሪያ ቤቱ አብረን ነን፡፡ አንዳንዶቹ ሀፍረት እሚባል ነገር በጭራሽ አያውቁም፡፡ እነማንዴላና እነፍሬድሪክ ደክለርክ በገረሰሱት የደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ ውስጥ የነበሩ ፈረንጆች ሀፍረት አያውቁ ይሆን? ‹ይሄ ገንዘብና ሥልጣን የማፈሪያችንን የሰውነት አካል ያበሰብስና ከሥራ ውጪ ያደርግ ይሆን?› እያልኩ መጠራጠር ይዣለሁ፡፡ በአዲስ አበባ የአንዳንድ (አንዳንድ ልበል እንጂ ምን ላድርግ!) አዎ፣ የአንዳንድ ትግሬዎችን አኳኋን ስመለከት ሰው ሆኜ በዚያም ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ መፈጠሬን እጠላለሁ፡፡ ለጥቅም ሲባል ከሰውነትና ከኢትዮጵያዊነት በፊት እንዴት ትግሬነት ወይም አማራነት ወይም ኦሮሞነት ሊቀድም ይችላል? ይህን እውነት ማመን ይከብደኛል፡፡ ትናንትናና ከትናንት ወዲያ እንዲያ የራሴ እላቸው የነበሩ ወንድሞቼ ለዚህ እንደጉም በንኖ ለሚጠፋ የብኩኖች ሥርዓት በደምና በአጥንት ምልኪ ተበርዘውና በዚያም አምልኮታቸውን አጽንተው ፈጣሪንም ዘንግተው ለጥቅምም ተንበርክከው የማልሰማቸው መስሏቸው አንዳቸው ካንዳቸው ጋር ተቀምጠው በትግርኛ ሲሞዳሞዱብኝ ለጊዜው እርር ትክን እላለሁ፡፡ ቆይቶ ግን በሞኝነታቸው ተገርሜ ለነሱም ለኔም አዝናለሁ፡፡ ወይ የታሪክ ፍርጃ! ለካንስ ታሪክ ሲጣላ እንዲህ ያጃጅል ኖሯል? ቅጥ ያጣውን መጃጃላችንን ታዲያ ዕልባት ልንሰጠው ይገባል፡፡ ስደት ዋጋ የለውም፤ በመነጣጠል ሚደግና መበልጸግ ዋጋ የለውም፤ እንደአህያዋ ‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል›ማለትም ዋጋ የለውም፡፡ የዛሬ ክብረት ለነገ ውርደት እንደሚያመቻቸን መረዳት ተገቢ ነው - አለመላው ክብረት ማለቴ ነው፡፡ በብዙው እየታማችሁ የምትገኙ ትግሬ ወንድሞቼና እህቶቼም ነቃ በሉ፡፡ መሌ ገሞራው ሂሳቧን አወራርዳ ስትዘጋ እሚጎዳው ማን ሊሆን እንደሚችል አሁን ነው መገመት፡፡ ማስፈራራት አልወድም አላውቅበትምም፡፡ ነገር ግን ከሦርያና ከሊቢያ ከዚያም በፊትና በኋላ በተከሰቱ ዓለም አቀፍ ክስተቶች መማር እሚቻለው ቁም ነገር የተፈጥሮን ሕግ ማንም ሊቀይር የማይቻለው መሆኑን ነው፡፡ ‹ቅል ካያያዝ ይሰበራል› ይላል ጥንታዊ ብሂላችን፡፡ ፈጣሪ ደግሞ ሲፈትነን ወይም ሊለካን ሲፈልግ ቅልን ይሰጠናል፡፡ እንደሦርያውያን አላዊቶች ሁሉ ኢትዮጵያውያን ትግሬዎችም ቆንጆ ቅል ሊያውም አዳሜ በፍቅሯ እየተነደፈ እሚነሆለልላትና በሕልሙ ሳይቀር በሃሳብ ከሚፈጥረው ተቀናቃኝ ጋር በእምሃበ አልቦ ባዶ ጦር ሜዳ ላይ ሻምላ እሚገጥምባት ማለፊያ ቅል አግኝታችሁ ነበር፡፡ በጥሩ ሁኔታ ብትይዟት ቅሊቷ ሳትሰበር ዘመናትን አቋርጣ ከናንተው ጋር ልትኖር በቻለች፡፡ ግን ያሳዝናል አያያዙን አላወቃችሁበትምና ቅሊቱ ልትሰበር የቀራት ጊዜ እጅግ በጣም አጭር ነው፡፡ እመኑኝ በጣም አጭር ነው፡፡ ‹የጭንቅላት ሥጋ መብሰሉ ለማይቀር እንጨት ይፈጃል› እንደሚባለው ሆኖ በኢትዮጵያ እምብርት ሸዋ ላይ የተቀበቀበው ወያኔያዊ የአዙር አንከርት ትብታባዊ ጦር መስዋዕትነትን ቢጠይቅም መነቀሉ ግን ፍጹም ሊጠራጠሩት የማይገባ ተፈጥሯዊ እውነት ነው፡፡ ማን አባቱ ሊሰብራት እንዳትሉ ታዲያን፤ እንደኔ ራሳችሁ ናችሁ በአያያዝ ችግር ምክንያት የምትሰብሯት፡፡ ሰባሪ ደግሞ ከየትም ሊመጣ ይችላል፡፡ ትንቢት በራስ ላይም ይፈጸማልና! ከተራብ ለጠገበ መታዘኑም ለዚህ ነው፡፡

በእውኑ ይህ ዓይነቱ ነገር (ከፍ ሲል ስለአድልዖ የጠቀስኩትን ማለት ነው) ከእንስሳዊነትም የወረደ አይደለም ትላላችሁ? ነገርን የማስታምምበትና አዝዬ እሽሩሩ የምልበት የይሉኝታ አንቀልባዬ አልቋል፡፡ ስለዚህ ዶማም ይሁን አካፋ ያው ዶማና አካፋ ነው ከሚል ነው የሆድ የሆዴን የምነግራችሁ - ቢከፋኝ፣ የማደርገውንም ባጣ፡፡ በሀገራችን በፖለቲካው መድረክ ትግሬ ካልሆንክ አትታመንም፡፡ ትግሬ ከሆንክ በግልፍተኝነት የበታችህን - ማንንም - በጸያፍ ቃል ሳይቀር መሳደብ ሙሉ መብትህ ነው፡፡ የሌላ ዘውግ አባል የሆነንማ በስማም... ሙልጭ አድርገህ እንዳይሸፐ እንዳይለወጥ ጥምብርኩሱን አውጥተህ መሳደብ የትግሬነትህ ኢሚዉኒቲ ያላበሰህ መብትህ ነው፡፡ በውጪ ሀገር ያላችሁ አህዋተይ ተጋሩ እንዲህ ስል ስታነቡ(ቡ ትጥበቅ) ስም ለማጥፋት የተነሳሁ ይመስላችሁ ይሆናል፡፡ እውነቱ ይሄው ነው፤ ገመናን ማለባበስ አይጠቅምም፤ እስካሁን እንዳልጠቀመን ሁሉ፡፡ ይልቁናም ምን እናድርግ ነው ማለት ያለብን? ማፈሪያ ልጆቻችንን ከቤተ መንግሥት አውጥተን የፈራረሰችዋን ኢትዮጵያ በጋራ እንዴት እንገንባ ነው ጥያቀው መሆን እሚገባው እንጂ የተራቆተን በድን የወያኔ ገላ ለመሸፈን ቆላ

EthioLion.com

ደጋ ማለቱ አይጠቅምም፡፡ በዚህ አጋጣሚ ይህን ጽሑፍ የማታወጡ ድረ ገፆችም እውነቱን ማወቅ ለሚገባቸው ወገኖቻችን ለብቻቸው በአድራሻቸው ‹እንዲህ ያለ ጽሑፍ ደርሶናልና እባካችሁ አሟሟታችሁ እንዲያምር አድርጉ፤ በኢትዮጵያዊነቱ በሚኮራውና ለሃይማኖቱ እንስፍስፍ በሆነው  የትግራይ ሕዝብ ስም መነገዳችሁን አቁሙ፤ ከራሳችሁም ጋር ዕርቅ ፈጥራችሁ ጤናማ ሰው ሁኑ › በሏቸው፡፡

… በቀበሌም ይሁን በወረዳ በየትም ሥፍራ ለወያኔ ድጋፍ ካልሆነ ተቃውሞ ካሰማህ ባትሆንም ነህ - ምን? እነሱ የፈለጉትን፡- አሸባሪ - ነውጠኛ- ነፍጠኛ- ትምክህተኛ- አነግ - ኦብነግ- ግንቦት ሰባት - መስከረም ሁለት (ደርግ ማለቴ ነው) - የማይለጠፍልህ ታርጋ የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ የነሱን የዱሮ ስም ሳይቀር - የጠባብነትን የስድብ ካባ- ሊያለብሱህ ይችላሉ - እነሱ ምን ቸገራቸው ገንጣይ አስገንጣይ ቢሉህም ደንታ አይሰጣቸውም፡፡ ዋናው እሚሉት አይጥፋ፡፡  አለመቀደም ነው ነገሩ እባክህን…

የሦርያና የኢትዮጵያ ችግር እጅግ በጣም ተቀራራቢ ነው፡፡ የቦታና የማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ሥሪት ካልሆነ በስተቀር መሠረታዊ ልዩነት የለንም፡፡ እነሱ ትግሉን ጀምረውታል፡፡ ‹ከዘላለም ባርነት የአንድ ቀን ነጻነት› ብለው በመጣው ይምጣ የነጻነት ትግላቸውን እያጧጧፉት ይገኛሉ፡፡ በአንድ ዓመት ውስጥም ከ10000 ሕዝብ በላይ በጭራቁ የአሳድ መንግሥት እንደተጨፈጨፉ በሚዲያ ተገልጾአል፡፡ ይሁንና የነጻነታቸው መባቻም እንደተቃረበ ቅድም የተመለከትኳቸውን የቢሻራ እንግዶች ጨምሮ ብዙዎች የፖለቲካ ተንታኞች እየተነበዩ ነው፡፡ ድል ያለ መስዋዕትነት የለምና የነሱ መልክ እየያዘ ነው፡፡ የኛ ብቻ ነው አካሜሌ እንደሆነ የቀረው፡፡ እርግጥ ነው እኛ እንዲህ ፈዝዘን የቀረነው እንዲህ ዓይነት በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነ ችግር ደርሶብን ስለማያውቅ ደንግጠንና እምንሠራውን አጥተን ይመስለኛል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ጨቋኝና በዳይ መንግሥት እንጂ ወያኔን የመሰለ ወንድምን ከወንድም የሚከፋፍልና እሥርና ሞት ላንዱ ቅልጥምና ብርንዶ ለራሱና ለቤተሰቦቹ የሚሰጥ ገጥሞን አያውቅምና ለጊዜው ሁሉም ነገር ግራ ቢሆንብን አይፈረድብንም፡፡ ይህን ለማመን የሚከብድ ሀገራዊ ችግር በደንብ በማጤን አሁን ያለው ትውልድ ለራሱ ሲል አንዳች መፍትሔ በቅርቡ እንደሚፈልግለት በበኩሌ አምናለሁ፡፡ በኛ ዘመን አድልዖና በቀዬ መሰባሰብ ጭራሹኑ አልነበረም ለማለት ሳይሆን ልክ እንዳሁኑ መንግሥታዊ ተቋም ሆኖ በሽል ምንጠራ አንዱን ፈጽሞ የሚያገልልና ለእሥርና ለስደት ለሞትና ለቁም ሞታዊ ውርደት የሚዳርግ መንግሥትም ሆነ ተቋም አልነበረም፡፡ በዘርና በቋንቋ ሳይሆን በአካባቢ ልጅነትና በአብሮ አደግነት በተወሰነ ደረጃ መድሎ ይደረግ ነበር እንጂ ዐይኑን ያፈጠጠ የዘውገኝነት መድሎ በሀገራችን ታይቶ እሚታወቅ አይመስለኝም፡፡ ይህ የአሁኑ የወያኔ ግሪሣ ግን የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት ለራሱ አጫፋሪዎችና ለውጪ ዘራፊዎች አጋልጦ የሚችለውንና የሚበቃውን ያህል ከመዘመዘ በኋላ ነቀዝ እንደበላው በቆሎ ባዶ ቀፎዋን ትቶ ወደትግራይ ትግሪኙ ለመንጎድ ያቆበቆበ ይመስላል፡፡ ይህን መናገር ታዲያ ጥፋቱ ምን ላይ ነው? ‹ወያኔ የኢትዮጵያ ክፉ ቀን ደራሽ፤ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ የነጻነት ብርሃን ያሳዩ የዴሞክራሲ አባት፣  ወያኔ በዘር ተበጣጥቆ የነበረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍቅርና በመተሳሰብ ያሰባሰበ የፍቅርና የመተሳሰብ ፈር ቀዳጅ፣ ወያኔ ከትግራይና ከጎንደር መሬት እያመጣ ለደቡብና ለምዕራብ የሚያከፋፈል ቸር አባት፣ ወያኔ ከሰሜን ተወርውሮ መሃሉንና ዳሩን ነጻ ያወጣ የኢትዮጵያ ቼጉቬራ፣ ወያኔ ለጽድቅ ሲል በቁራሽ እንጀራ ነፍሱን እያሳደረ ለሕዝቡ ክትፎና ቁርጥ የሚያቀርብ የአፍሪካ ሆቺሚንና ሳንሱቺ ነው…› እያልን እንጻፍ ይሆን? ሞኞች! መቶ በመቶ እሚጥም አይገኝም ወንድሞች፤ እሚጥመው ይልቅስ ነገርን ከጎኑና ከበስተጓላው በሾርኒና በአግቦ ወይም በተንኮልና በሸር በተቃኘ ነባር የጥርጣሬና የአለመተማመን መንፈስ በመግባት ሳይሆን በገርነት ከበስተፊትና በቀጥታ ገብተው በቅንነት ሲመለከቱት ብቻ ነው፤ ያኔ ነው መግባባትና መተማመን የሚፈጠረው፤ የነገር ወጡ መደማመጡ ነው ዋናው ነገር፡፡ አለበለዚያ ያው የተለመደው ‹ እንካስላንትያ በብጣሽ› - ‹ምን አለ በድሪቶ› ዓይነት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ላይ የተመሠረተ መደነቋቆር ነው ትርፉ፡፡ ለነገሩ አንተ የምትለውንም አንተው ራስህ ትንሽ ቆይተህ ብትመረምረው እኮ ስንትና ስንት ገለባና ንፋሽ ታገኝበታለህ ወንድሜ፡፡ መጽሐፉም ይላል፡- ‹ሰው ሰደበኝ ክፉ ነገርም ተናገረኝ ብለህ በቀላሉ አታኩርፍ - አትቀየምም፤ የሰውንም እንደበት ይሁነኝ ብለህ አትከታተል፡፡ ሌሎች በሚናሩት እንዲያ በቀላሉ የምትከፋ ከሆነ አንተም ከምትናገረው ብዙው ሲታይ ሌሎችን የሚያስከፋ መሆኑ አይቀርምና በማስተዋል መራመድን ልመድ፡፡›… የሦርያና የኢትዮጵያ መመሳሰል ግን አይገርምም? ድንጋይን ምን ያናግረዋል ቢሉ ውኃ አሉ፤ እኔንም አልጀዚራ ስሜቴን ቆፍቁፎ በሰንበት ምድር ምሬት አናገረኝ፡፡ ይሁን፡፡ ምን ይደረጋል? የፈሰሰ አይታፈስም፡፡ እስኪያልፍ ማልፋቱ ከፋ እንጂ ሁሉም ነገር ያልፋል - ዓለምም ጭምር፡፡ እናስ ምን ሊቀርብን?

EthioLion.Com